# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-31/2017 የነበረው
# የአየር ጠባይ ግምገማ


ባለፈው የኦክቶበር ወር በመካከለኛው፣ በሰሜንና በምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በአብዛኛው የበጋው ደረቃማው የአየር ሁኔታ አመዝናባቸው የቆየ ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞም በተለይም በጥቂት ሥፍራዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደጨመረ ይታያል፡፡ በዚህም መሰረት ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች በተለያዩ ቀናት ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል በቡኢ 4.6" 4.5 እና 4.0፤ በደብረ ብርሃን 4.0 እና 3.6፤ በወገል ጤና 2.4 እና 1.7፤ በአምባ ማሪያም 4.5 እና 2.5 እንዲሁም በመሐል ሜዳ 3.0 በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል በወሩ ውስጥ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአብዛኛው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የነበረ ሲሆን፤ በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይም ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ. በላይ ከባድ ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል በአቦቦ 49.2፣ በላይበር 38.9፣ በአርጆ 36.4፣ በዲላ 34.7፣ በአይከል 30.1፣ በቦሬ 30.0. በጅንካ 51.3፣ በቡለን 51.1 እና 30.6፣ በሻውራ 32.2፣ በግምቢ 43.9፣ በማጂ 50.0 እና 33.6፣ በሊሙገነት 38.6፣ በጨዋቃ 55.4፣ በኢጃጂ 33.2፣ በበደሌ 34.8፣ በጭራ 38.9፣ በቀብሪደሀር 50.0፣ በሐገረ ማርያም 48.7፣ በአይራ 46.2፣ በጋምቤላ 45.6፣ በማይፀምሪ 42.7፣ በጂማ 33.5፣ በዳንግላ 32.4፣ በፓዌ 33.4፣ በሞጣ 33.8፣ በሴሩ 32.5፣ በፉኚዶ 31.5፣ በኮንሶ 30.5፣ እንዲሁም በጠርቻ 30.2፣ በሚ.ሜ. ይገኙበታል።

ባለፈው ወር የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ25-283 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ የምዕራብና የደቡብ ትግራይ፤ ከአማራ ሰሜን ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አገዋዊና የደቡብ ወሎ ሰሜናዊው ክፍል፤ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ ጋምቤላ፤ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፤ አብዛኛው ሶማሌ፤ ከኦሮሚያ ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጂማ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲና ባሌ እንዲሁም የቦረና ዞኖች እና አብዛኛው ሶማሌ ከ5-28 ቀናት ያህል ዝናብ ያገኙ ሲሆን፤ የምስራቅ ትግራይ፤ ከአማራ ዋግህምራ፣ ሰሜን ወሎ፣ መካከለኛው እና ምስራቅ አማራ፤ ከኦሮሚያ ሰሜንና ምሥራቅ ሸዋ፤ እንዲሁም ከአፋር ጥቂት የዞን 1 ደቡባዊው ክፍል ደግሞ ከ5-25 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከ5 ላነሱ ቀናት ያህል የተመዘገበ ሲሆን፤ አብዛኛው አፋርና ድሬዳዋ ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 6 እና 7) ።


በወሩ ውስጥ የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር የምዕራብና የደቡብ ትግራይ፤ ከአማራ ሰሜን ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አገዋዊና የደቡብ ወሎ ሰሜናዊው ክፍል፤ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ ጋምቤላ፤ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ አብዛኛው ሶማሌ፤ ከኦሮሚያ ምዕራብና የምሥራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጂማ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲና ባሌ፣ የቦረና ዞኖች እና አብዛኛው ሶማሌ እንዲሁም ከአፋር ጥቂት የዞን 1

ደቡባውው ክፍል መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ያገኙ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛው ያነሰ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ8)።


ካርታ6   እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ7   እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ8   እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# <u>እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-31/2016 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

ባለፈው የኦክቶበር ወር በመካከለኛው፣ በሰሜንና በምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በአብዛኛው የበጋው ደረቃማው የአየር ሁኔታ አመዝናባቸው የቆየ ነበር፤ ይህም በመሆኑም በተለይም በመደበኛ ሁኔታ ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍል ዝናብ መውጫው ስለሆነና በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሄዱ በአንዳንድ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ቢሆንም፤ በተለይም በአንዳንድ ለውርጭ ተጋላጭ በሆኑ ሥፍራዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እየጨመረ በመምጣቱ እድገታቸውን ባልጨረሱ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ጎን ሊያሳድር ይችላል። በሌላ በኩል በወሩ ውስጥ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ በመኖሩ ምክንያት የተገኘው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም የተገኘው እርጥበት በአካባቢው በዝናብ መቆራረጥ ምክኒያት ተገልብጠ በድጋሚ ለተዘሩ ሰብሎች አሉታዊ ተፅእኖ ነበረው። በአንጻሩ ደግሞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ፤ የተገኘዉ እርጥበት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ እንደነበረው እሙን ነው (ካርታ 9)።

ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2017 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ




# <u>እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-31/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>

# <u>በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደርው ተፅዕኖ</u>

እ.ኤ.አ 1-31 ኦክቶበር2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ምስራቅና በደቡባዊ የአገሪቱ አጋማሽ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል$ በዚህም መሰረት ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች የአባይ ምዕራባዊ አጋማሽ፣ አብዛኛው ባሮአኮቦና ገናሌዳዋ፣ የታችኛው ተከዜ፣ እንዲሁም የመካከለኛውና የታችኛው የኦሞጊቤ ፣የዋቢሸበሌ፣ የኦጋዴንና የስምጥሸለቆ፣ ተፋሰሶች ናቸው$ በተጨማሪም በከፊል የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ በጥቂት የላይኛው ስምጥሸለቆና ኦሞጊቤ፣ የአባይ መካከለኛውና ምስራቃዊው ክፍልና፣ የተከዜ ምዕራባዊውና የታችኛው ክፍል ተፋሰሶች ደግሞ መጠነኛ እርጥበት የተሰተዋለባቸው ናቸው$ በኦክቶበር ወር በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ከባድ ዝናብ በጥቂት ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የተመዘገበ ሲሆን፤ ይህ ሁኔታ ለዉሃ ሀብት ግብኣት በመሆን ጠቃሚ ገፅታ ነበረው (ካርታ 10)።

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2017 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## <u>እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-30/2017 የሚኖረው</u>
## <u>የአየር ጠባይ አዝማሚያ</u>

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ከማመዘኑ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት የሚታይበት ሲሆን፤ ከዚህም ሌላ በተዳከመ ሁኔታ ቢሆንም እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ አጋማሽ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ እየዘነበ ይቆያል።

በሚቀጥለው ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ የአየር ጠባይ እንደሚስተዋል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥለው ወር ደረቃማ የአየር ጠባይ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተጠናክሮ እንደሚቆይ ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጨምር እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፤ በጥቂት ደጋማ ቦታዎችም ላይ ውርጭ ሊከሰት ይችላል። ከዚህም ሌላ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል።

በመሆኑም በሚቀጥለው ወር <u>በአብዛኛው የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተጨማሪም በአንዳንድ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠናከር እንደሚችል ይጠበቃል። ከዚህም ሌላ ከኦሮሚያ ዞኖች ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ እንዲሁም የጉጂ እና የቦረና፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳና የከማሺ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ሕዝቦች፤ በሶማሌ ክልል የሚገኙት የደገሀቡር፣ የፊቅ፣ የዋርዴር፣ የቆራሄ፣ የአፍዴር፣ የጎዴ እና የሊበን ዞኖች በተለያዩ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በአንጻሩ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ።</u>

## <u>እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-30/2017 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ</u>
## <u>በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በመደበኛ ሁኔታ የኖቬምበር ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት አከባቢዎች የመኸር ሰብሎች ፍሬ የሚያፈሩበትና በአንድ አንድ አከባቢዎች ደግሞ ሰብሎች የእድገት ጊዜያቸውን ጨርሰው ለመሰብሰብ የሚደረሱበት ወር ነው፡፡ በሚቀጠለው የኖቬምበር

ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚጠናከር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተጨማሪም በጥቂት ደጋማ ቦታዎች ላይ ውርጭ ሊከሰት እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም ደረቅ ሁኔታ የእድገት ጊዜያቸውን እየጨረሱ ላሉና ተጨማሪ የውሃ አቅረቦት ለማይፍልጉ ሰብሎች እንዲሁም የእድገት ጊዜያቸውን ጨርሰው ለመሰብሰብ ዝግጁ የሆኑ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ፤ በጥቂት ደጋማ ቦታዎች ላይ ሊከሰት የሚችለው ውርጭ ዘግይተው ለተዘሩትና ፍሬ ማፈራት ደረጃን ያላለፉት ሰብሎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በተዳከመ ሁኔታ ቢሆንም እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩትና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱት የመኸር ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ አቅርቦት ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሩና ለከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢዎች ለመጠጥ ውሃ ቅርቦት መሟላትና ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ መሻሻል ምቹ ሁኔታን ይፈጠርላቸዋል፡፡

## እ. ኤ. አ ከኖቬምበር 1-30/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኖቨምበር ወር ውስጥ በአብዛኛው የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅና ፀሃያማ ሁኔታ የሚያመዝን ቢሆንም፤ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ  የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት የሚስተዋልበት ወር ነው$ ሆኖም በብዙዎቹ ተፋሰሶች ላይ በሚኖረው ነፋሻማና ፀሃያማ የአየር ሁኔታ የውሃ ትነትን ስለሚጨምር ያለውን የውሃ መጠን እየቀነሰ በመሄድ ደረቅ ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል የጠበቃል$ ይህንን ተከትሎ በሰሜናዊው የሀገሪቱ አጋማሽ በሚገኙት ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሃማና ነፋሻማ ሁኔታ ቢያመዝንም በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ገናሌዳዋ፣ ዋቢሸበሌ፣ የአባይ ደቡባዊ አጋማሽ ክፍል፣ የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥሸለቆና የኦጋዴን ተፋሰሶች በአብዛኛው በተለያዩ ቦታዎቻቸው ላይ መደበኛ የሆነ ዝናብ እንደሚያገኙ ትንበያው ይጠቁማል$ ይህም ሁኔታ በተለይ በደቡብና በደቡብ ምስራቅ በሚገኙ በመካከለኛውና በታችኛው ተፋሰሶች ላይ ዝናብ መኖር የውሃ እጥረትን ለመቅረፍ አስተዋፆ ከማድረጉም በላይ ለከርሰ ምድርና ለገጸምድር የውሃ ክምችት መጨመር አስፈላጊ በመሆኑ ተፋሰሶች ላይ የተለያዩ የተፋሰስ ስራ ማከናወን ተገቢ ነው፡፡